# “ብር አምባር ሰበረልዎ” *ገላነው-ክራር*

“... ደራሲ sensitive (ስሜታዊ?) ነው” የሚል ማንበቤ ትዝ ይለኛል፡፡ የፈጠራ ስራ (ሲኒማ፣ ትያትር፣ መጽሃፍ ...) የሚመዘነው ባብዛኛው በገጸ ባኀርያቱ ውስጥ በምናየው የድርጊት/ባህርይ/ሃሳብ ...ተቃርኖ (contrast?) ነው፡፡ ለምሳሌ ጥሩ አድራጊው እና መጥፎ አድራጊውን ጥሩ ወይም መጥፎ የሚያሰኛቸው የጥሩ ወይም መጥፎ ድርጊታቸው፣ ባህርያቸው እና/ወይም ሃሳባቸው ተቃርኖ ጡዘት ነው፡፡ (የኦቴሎን ደግነት፣ ጀግንነት፣ ግልጥነት እና የእያጎን መሰሪነት፣ ክፋትና ምቀኝነት.... እስከ የት ጥግ እንደሆነ ተቃርኖውን (contrast) ልብ ይሏል)፡፡ እና ደራሲ ከራሱና ከሌላው በማናቸውም መንገድ እና ሁኔታ በህይወቱ ከሚያውቃቸው አጋጣሚዎች፣ በዕውኑ ዓለም ያሉ ሰዎችንም ባህሪ፣ ድርጊት፣ ሃሳብ...ወዘተ ከራሱ ባህሪ ድርጊት፣ ሃሳብ እና ስሜት (emotion? feeling?) ጋር እያዋሀደ ነው—መልሶ ጽፎ የኛን የተደራሲዎቹንም ስሜት ወጥሮ የሚይዘው፡፡ ደራሲ ገና “እየፈጠረው” ያለው “ሰው” ሲታመም ይታመማል፣ ሲያለቅስ ውስጡ *(አንዳንዴም ዕንባ አውጥቶ)* ያለቅሳል፣ ሲደሰትም አብሮ በደስታ ይፈነድቃል፡፡ ስለዚህ ደራሲ በዕዉኑ አለም ክስተቶችም ከመደዴው (ordinary) ሰው በተለየ ስሜታዊ ነው ቢባል አልተጋነነም፡፡

ከሰሞኑ በኢትዮጵያ ስነ-ፅሁፍ ታሪክ ትልቅ ስም ካለው ደራሲ ጋር ከቡና ጋር ወሬ ይዘን ነበር፡፡ ወሬያችን በስነ-ጽሁፍ ተጀምሮ ፖለቲካ፣ ሃይማኖት... ውስጥ ገባ፡፡ ደራሲው ለኔ ተንቀሳቃሽ ቤተ-መጽሃፍት ነው፡፡ “ደራሲ መሆን ከፈለግህ ግማሹን ቤተ-መጽሃፍት አንብብ...” የሚሉ አባባል አውቃለሁ፡፡ እና “መዱስ” (መጽሃፍ-ቅዱስ) ስለያዘው “ጉድ”--ባርነትን እና በሴቶች ላይ የሚደርስ በደልን እንዴት እንደሚያበረታታ ... ከሚያውቃቸው ምዕራፎቸ አንቅጽ በአንቀጽ እየጠቀሰ ነበር ያብራራልኝ፡፡ ስንቱን እዘረዝረዋለሁ እዚህ?....... እናም ስናነሳና ስንጥል፣ ስንቆርጥና ስንቀጥል ቆየንና ስለ አጥፍቶ ጠፊዎቹ (suicide bombers) አስተሳሰብ (mind set) ስለ አደገኛነቱ፣ እና *መስዋዕት;*”martyr” ጀሃዲስቶቹን መ/ሰማያት ውስጥ ስለሚጠብቋቸው 72 ደናግል ቆነጃጂት አነሳሁበትና ... ***“ለመሆኑ መ/ሰማያት ውስጥ ሰማዕቱን ስለሚጠብቁዋቸው ደናግል ጉዳይ ቁርአን ውስጥ የተጠቀሰውን ቃል በቃል ታውቃለህ?”*** ስል ጠየቅሁት፡፡ አልመለሰልኝም፡፡ ቁዝም ብሎ ቀረ፡፡ እንዲቆዝም ፈቀድኩለት-- በዝምታዬ፡፡ እናም እኔም ቁዘማ ገባሁ—ቢን ላደንን ይዤ፡፡

ለነገር ነገሩ ግን ይሄ ቢን ላደን ማለት የዋዛ ጮሌ አልነበረምና! እሱ አንድ አይሉ ሦስት ሚስቶቹ ጋር አለማዊ አለሙን እዚሁ አለም ላይ እያየ፣ ‹ሰማያዊ ሰማያት ውስጥ ያለ መንግስተ ሰማያት ውስጥ 72 ደናግል ይጠብቁዋቾኋል! ገድላችሁ ሙቱ› እያለ ልጅ ልጁን ይልካል፤ ያስልካል፡፡ *(በአጥፍቶ መጥፋት የተሰማሩ ሰዎች ማንነት (ዕድሜ፣ ትምህርት  ወዘተ...) መረጃ ቢሰባሰብ፣ በቁጥር ብዛት ቁንጮውን ስፍራ የሚይዙት እንቦቀቅላዎቹ--በአሰርቶቹ መጀመሪያ ውስጥ ያሉ ታዳጊ ወጣት ልጆች፣ ዘመናዊ ትምህርት ብዙም ያልዘረባቸውና፣ በድህነት ያደጉ ይመስሉኛል፡፡ አለመማር እና ድህነት ከአምልኮ ጋር ያላቸው ትስስርም የዋዛ አይደለም፡፡ በመለስ አገዛዝ የዘር ፖለቲካ እየታሸ፣ በሀይማኖት ልዩነት እየታመሰ ... እና ወደ ማይምነት እና ድህነት ጥግ እየተገፋ ያለውን ህዝብ ብዛትና ማንነት (identity) ሳስበው....... አንዳንዴ እንዲህ ያለ ነገር ሳስብ ራሴን ጸለምተኛ (pessimist) ስለሆንኩ ይሆን ?  እል ነበር፡፡ ደራሲው አገራችን ውስጥ ሊከሰት ይችላል ያለውን ትንበያውን፣ እዚህ ለመጻፍ የምደፍረው ጉዳይ አይደለም፡፡ በሱ አንጻር እኔ በጣም አብርሆታዊ (optimist)  ነኝ፡፡ መሬት ላይ እየሆነ እና እያየነው ያለው ያስፈራል፡፡ የመለስ መንግስት እድሜ በተራዘመ ቁጥር፣ ዛሬ “አነግ ተገንጣይ ነው“... “አብነግ ድብቅ አላማው መገንጠል ነው...“  የምንለው ሁሉ እንቶ ፈንቶ የሚሆንበት ቀን ላይ እንደርሳለን፡፡ እየየም ሲዳላ ነው፡፡ (ይህን በተመለከተ ከሰሞኑ በሰፊው እመለስበታለሁ፡፡)*

... እናም ተመልሼ ቢንላደንን ይዤ ... ደሞ ላንድ ጎረምሳ የሚሰለፉትን የሰባ ሁለቱን ደናግል ጉዳይ በሃሳቤ ሳወጣና ሳወርድ ደራሲው ድንገት ጉሮሮውን ጠራርጎ ***...“አንድ ያየ እንዴት ሰባ ሁለት ይመኛል?”*** ብሎ ነበር ከቁዘማዬ የገላገለኝ፡፡ ቅድም ቁዝም ብሎ ሲቀር፣ በጉርምስና እድሜው፣ ያኔ የሆነው፣ የልጃገረድዋ ... በጆሮው ሳያቃጭልበት ይቀራል?

ባንድ ወገን “ብር አምባር ሰበረልዎ” እያለ እና እያስባለ በሚጨፍር እና በሚያስጨፍር፤ ... የሴት ልጅ ደም በነጭ ሻሽ ተጠቅሶ፤ በሙዳይ ተይዞ... ህመምና ስቃይዋ የሚያስጨፍረው ማህበረሰብ አባላት—እኛ መደዴዎቹ (ordinary people) አለን፡፡ በሌላው ወገን ደግሞ እንዲህ ያለ ማህበረሰብ ውስጥ፣ እንዲህ አፈንግጦ የወጣ፣ የደራሲው “ስሜታዊነት”—ውብ ሰብእና አለ፡፡ ... ልጠይቅህ ...አንተን ወንድሜን... የልጃገረዱዋን ህመም እንዲህ ታመህላት ታውቃለህ?...  እውነትም “ደራሲ ስሜታዊ ነው”፡፡...

## ማሳረጊያ፡-

የድንግል ነገር ቢነሳ፣ አያ ከልክሌ እና ድንግል ማርያም ትዝ አሉኝ፡፡ እንዲህ ሆነ፡፡ ቀትር ላይ ባልተለመደ መልኩ ተኮረብታው ማዶ አቅጣጫ ኡኡታ ይቀልጣል፡፡ ድፍን ያጥቢያው ሰው እየተቀባበለ “ጉድ”  እያለ ኡኡታውን እያዳረሰው ወደዚያው ተመመ ፡፡ በርቀት ጢስ ይታያል፡፡
“‹የከሌ አባበሉ ቤትኮ እዚያ ነው› ይላል” አንዱ፡
“የለ! የማንትስ ያውድማ ላይ ክምር ነው አሉ የተቃጠለው...” ሌላው፡፡
“ኸረ የማርያም ቤተስኪያን እዚያም አለ! ...”  ይሄኛው ሰምሮለታል፡፡ የምየ ማርያም ቤተስኪያን እየተቃጠለ ኖሩዋል፡፡ እሳቱን ማንም ሊቆጣጠረው አልቻለም፡፡... ቀድመው ደርሰው ተሳቱ ሲታገሉ ከነበሩት ውስጥ አንዱ፣ አያ ከልክሌ ተስፋ በቆረጠ ሁኔታ የሚንቀለቀለውን እሳት እያስተዋሉ፣ እሳቱን ለማጥፋት አለመቻሉ እየጸጸታቸው፣ ኣንዳንዴም ... ወትሮስ የገዛ ልጅዋ ያልደረሰላትን አሁን እኔን “እማምላክን ተሳት አላዳንኪም” ብሎ ማን ያማኛል?...፡... ታዲያ ለገዛ እናቱ ያልሆነ አሁን ለኔ...፡፡
የደረሰ አዝመራቸውን፣ ሌላ ጊዜ በመከራ የቀለሱዋት ጎጆዋቸውን፣ ሲሻው ያውድማውን ክምር እያቃጠለ፣ እና እያነደደ...አንጀታቸውን አሳርሮ ኖሮ፡-

**“እዚያ ላይ ተቀምጠህ ስታላግጥ በሰው**
**እናትህ ነደደች አዘንን ቅመሰው*፡፡”** **ብለው እርፍ!**

Gelanew-kirar@hotmail.com

** Fikade Azeze: 1998 “Unheard voices” p.102*